# ቤተመቅደስና ታቦት

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሰማይ ዙፋኑ ምድር የእግሩ መረገጫ ቢባልም እርሱ ግን ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት የነበረ በሁሉ የመላ ረቂቅ አምላክ ነው።

ይህ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ፍጥረቱ የሆነው የሰው ልጅ እርሱን ያመልክበት ዘንድ ማደሪያዬ ብሎ ቤተመቅደስ ይሰሩለት ዘንድ የሰው ልጆችን አዝዟል።

"በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ" ዘጸ. 25፥8

"ማደሪያዬንም በእናንተ መካከል አደርጋለሁ" ዘሌ 26፥11

ይህንን የእግዚአብሔር ቃል የሰሙና የፈፀሙ ቅዱሳን ትእዛዙን አክብረው የእግዚአብሔርን ማደሪያ ሰርተዋል - ለምሳሌም ፦

ሀ. በሙሴ የመገናኛው ድንኳን

ለ. በሰሎሞን የቤተመቅደሱ ሕንፃ

ይህ ሁሉ ደግሞ በሰማይ ባለው አምሳል ነበር።ነው።

"እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት" ዘጸ 25፥9

ልዑል እግዚአብሔር ቤተመቅደስ በሰው ልጆች ለመገለጫው ለማደሪያው ይሠራለት ዘንድ የፈቀደው እርሱ ነውና በዚህ ቤት የሚለምኑትን ሁሉ እሰማለሁ፣ ቤቴ የጸሎት ነው፣ ለዘላለም በዚህ አድራለሁ ብሏል። ለሰሎሞንም የነገረው ይህንን ቃል ኪዳን ነበር።

"እግዚአብሔር አለው .... ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።" 1ነገ 9፥1-4

በእግዚአብሔር ቤት ሰዎች ሁሉ ክብርን በመስጠት፣በመፍራት፣ጫማን በማውለቅ ይገቡ ዘንድ በዚያም ከጸሎት ከልመና በስተቀር ከሌላ ከዓለማዊ ነገር ሁሉ እንርቅ ዘንድ እግዚአብሔር ያዛል

ማቴ 21፥12 "... ቤቴ የፀሎት; ቤት ትባላለች ..."

ዘሌ 26፥2 "መቅደሴንም ፍሩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ"

አንባቢዎች ሆይ እግዚአብሔር አዟልና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ በጥንቃቄ ይሆን ዘንድ ይገባዋል።ጥንቃቄውም እንዲህ ነው።

ሀ. ጫማ አድርጎ መግባት አይፈቀድም

ለ. ሴቶች በልማደ ሴዋን ጊዜ (በወር አበባ) መግባት አይፈቀድም

ሐ. ወንዶች ሕልመ ሌሊት ሲያጋጥማቸው መግባት አይፈቀድም

መ. ለሐጩን መቆጣጠር የማይችል ሕመምተኛ (መዝረብረብ) ያለበት መግባት አይፈቀድለትም

ሠ. ባልና ሚስት ዕለቱን ግንኙነት አድርገው መግባት አይፈቀድም

ረ. ይህን የመሳሰሉ

አስረጅ - ዘጸ. 3፥5 ሐዋ.7፥33 ኢያሱ 5፥14 ዘሌ.12

እግዚአብሔር አምላካችን የሰጠንን ትዕዛዝ በምንጠብቅበት ጊዜ በረከቱና ጸጋው ለሁላችን ነውና ቤተክርስቲያን ጸጋ የምንለብስባት ከኀጢአት እስራት ነፃ የምንወጣባት ናት።በቤተመቅደስ ቤተክርስቲያን ጌታችን አለ፣ ቅዱሳን አሉ፣ መላእክት አሉ - ይህም የመገናኛ ድንኳን ይባላል።

አስረጅ - ዘጸ 29፥42 ሐዋ 2፥46 ሐዋ 3፥1 ራዕ 21፥3

በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚገለጥበት ታቦቱ ስለአለ ነው ቤቱ የከበረው።

**ታቦት**

ቤተመቅደስን ቤተመቅደስ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚያሰኘው የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው።ይህ በሰው ፈቃድ የተደረገ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሰው ልጅ ያደርገው ዘንድና እሱን ያመልክበት ዘንድ የተሰጠ ነው።ይህም ሰውና እግዚአብሔር ይገናኙበት ዘንድ ነው።

ትርጉም፦ ታቦት - እንደ ሳጥን ያለ የጽላት መያዣ ሲሆን

ጽላት- ደግሞ ሕጉ የተቀረጸበት ነው

ይህ በእግዚአብሔር ለዘላለም ቃል ኪዳን ይሆን ዘንድ ለሕዝቡ ማምለኪያ በሙሴ አማካኝነት የተሰጠ ነው።

"እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ
በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር
ጽላቶች ሰጠው።" ዘጸ. 31፥18

እግዚአብሔር ማደሪያው የሆነውን ይህንን ጽላት ለሙሴ የሰጠበት ምክኒያት-

ሀ. ሙሴ በጣም ትሁት በመሆኑ - ዘፍ. 12፥3

ለ. ያመኘና ጸሎተኛ በመሆኑ ዘዳ. 9፥9

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በመጀመሪያ የተቀበለው የምስክር ጽላት በእስራኤል ኀጢአት ምክኒያት ቢሰበርም በምትኩ ሌላ ይሰራ ዘንድ እግዚአብሔር አዝዟል። ይህም ታቦትን ቅዱሳን ሰዎች ሊቀርጹት እንደሚችሉ የእግዚአብሔር መልአክት ያሳያል።

"እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ ሁለት ጽላቶች እንደፊተኞቹ አድርገህ
ጥረብ፡በሰበርኸቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ"
ዘጸ. 34፥1

<u>*ታቦት ኃይል ፡ የእግዚአብሔር ታቦት ለሚያምኑት ኃይል፣ በረከት ነው። ለማያምኑትና ለሚነቁት ግን የሚበላ እሳት ነው።*</u>

- መ. ኢያሱ 3፥15 ፦ "ታቦቶቹንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ"
- መ. ኢያሱ 6 ካህናት ታቦቱን ይዘው 7 ጊዜ ሲዞሩ ኢያሪኮ ወደቀ
- መ. ሳሙ. 5 ፍልስጤማውያን የእግዚአብሔር ታቦት ጣዖት (ዳጎን) ቤት ንቀው ቢያስገቡት ታቦቱ ጣዖቱን ሰባበረው
- 2 መ. ሳሙ. 6፥6-9 ያዛ ስልጣነ ክህነት ሳይኖረው ታቦቱን በድፍረት ቢነካ ተቀጣ ፡ተሰበረ
- 2 መ. ሳሙ. 6፥20-23 ቅዱስ ዳዊት ለታቦት ቢዘምር ሚስቱ ሜልኮል ብትንቀው እግዚአብሔር የሜልኮልን ማህፀን ዘጋ።

**የታቦት ዘላለማዊነት**

እግዚአብሔር አምላክ ይህንን ቅዱስ ማደሪያውንና መገለጫውን ለሙሴ ሲሰጥ ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ቃል ኪዳን አድርጎ ነው።ምክንያቱም በላዩ የሚገለጠው አልፋ ኦሜጋ የዘላለም አምላክ ስለሆነ የማያምኑ ሰዎች ታቦት በብሉይ ኪዳን እንጂ በአዲስ ኪዳን ተሽሯል ይላሉ።የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ግን ምን ይላል?

ማቴ. 5፥17 "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም

እንጂ ለመሻር አልመጣሁም”

ስለዚሁም የቃል ኪዳኑ ታቦት የተሻረ ነው ብሎ የሚያስብ ከወንጌሉ ውጪ የሆነና የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፍ ነው።እኛ ግን እናከብረዋለን የሚገርመው የእግዚአብሔር የቃልኪዳኑ ታቦት እንኳን በምድር በሰማይ ቤተመቅደስ አለ። የዘላለም ፣ የማያልፍ ፣ የማይሻር የእውነት ኪዳን ነውና።

“በሰማይም ያለው እግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ” ራዕ 11፥19

## ታቦት በቅዱሳን ስም

በመሠረቱ ሰው ሁሉ ሊያውቀው የሚገባ ታቦት የእግዚአብሔር ነው።ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ እየደጋገመ “የእግዚአብሔር ታቦት” “የእግዚአብሔር ታቦት” የሚለው።

አስረጅ - ዘጸ.32፥16፣ 1ሳሙ.6፥1

ታዲያ በቤተክርስቲያናችን ስለምን የእመቤታችን የሚካኤል፣ የተክለሃይማኖት፣ የዮሐንስ የመሳሰሉት ታቦት ነገሠ፣ ወጣ ተከበረ የምንለው። ነገሩ እንዲህ ነው። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ስለሱ የኖሩትን፣ ዓለምን ንቀው የተከተሉትን፣ ስለሱ መከራ የተቀበሉትን፣ ቃል ኪዳኑን ስለጠበቁት የተመረጡ ሰዎች የተናገረውና ቃል የገባው ኪዳን አለ።ይህም በራሱ ቤት ላይ የዘላለምን የማይጠፋ ስምን እንደሚሰጣቸው አንዱ ማደሪያው ቤቱ የቃል ኪዳኑ ታቦት ነውና በዚያ ላይ ስምን ሰጥቷቸዋል።

“... በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፡ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋሁ...” ኢሳ. 56፥4-7

ልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳንን በባረከበት በረከቱ እኛንም ይባርከን፡ አሜን!